የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

**OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA**

ሰላሳ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፺፭
አዲስ አበባ የካቲት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**33th Year No .95**
**Addis Ababa 8th February, 2025**


**ማውጫ**


**ደንብ ቁጥር ፻፹፭/፪ሺ፲፯**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የወጣ ደንብ**

**ገጽ** ……………………………………..፫ሺ፰፻፺፮


**CONTENT**


**REGULATION No.185/2025**
**A REGULATION TO MAKE IT GIVE THE COMMERCIAL AND TRANSPORT SERVICES IN THE EVENING**

Page… ……………………………3896


## ደንብ ቁጥር ፻፹፭/፪ሺ፲፯
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የወጣ ደንብ

የአዲስ አበባ ከተማ አሁን ከደረሰችበት ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ ለውጥ አንፃር የአብዛኛው ማህበረሰብ የሥራ ባህል እና ፍላጎት በመለወጡ የንግድ ሥራዎችንና አገልግሎቶችን በምሽት መከወን እየተለመደ የመጣውን ተግባር ወጥነትና ቀጣይነቱን ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በከተማዋ በስፋት እየተከናወነ የሚገኘው መሠረተ-ልማት በኢኮኖሚው ላይ የፈጠረውን መነቃቃት አጠናክሮ ለማስቀጥል፣ የሥራ ባህልን ይበልጥ ለማዳበር፣ የኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን፣ የከተማዋን ተወዳዳሪነት እውን ለማድረግ ቀን ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ በምሽት የንግድ እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤

## REGULATION No.185/2025
## A REGULATION TO MAKE IT GIVE THE COMMERCIAL AND TRANSPORT SERVICES IN THE EVENING

**WHWREAS,** it has become necessary to ensuring the consistency and continuity of the activities that are becoming more common to treat commercial activities and services in the evening given the economic and social change of the city of Addis Ababa has now experienced, the working culture and needs of most of the community have changed;

**WHWREAS,** it has become necessary to create a comfortable environment where commercial institutions and service providers are serviced in the evening in addition to day-long services to realize the city's competitiveness the city's widespread infrastructure is being used to intensify its resurgence in the economy, to further develop a working culture, to accelerate economic growth;

በከተማዋ መንገድ ዳር ያሉ የንግድ ቤቶች እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚያበሯቸው ስታንዳርዳቸውን የጠበቁ መብራቶች የአካባቢውን ውበት ይበልጥ የሚያደምቁ እና ሠላምና ፀጥታ ለማረጋገጥ አጋዥ በመሆናቸው ህብረተሰቡ ለመዝናናትና እረፍት ለማድረግ የሚያዘወትራቸው ተመራጭ ቦታዎች እንዲሆኑ ለማድረግ፤

የንግድና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተቋማት በምሽት ተግባራቸውን ማከናወን የሚችሉበትን የአሰራር ሥርዓት በህግ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ካቢኔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፹፬/፪ሺ፲፯ አንቀጽ ፺፬ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "በምሽት የንግድ እና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የወጣ ደንብ ቁጥር ፻፹፭/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ ደንብ ውስጥ የቃሉ ወይም ሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

፩. **"ከተማ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ነው፤

፪. **"የከተማ አስተዳደር"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፤

፫. **"ቢሮ"** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ነው፤

፬. **"ነጋዴ"** ማለት ንግድን የሙያ ሥራው አድርጎ ተገቢ ጥቅም ለማግኘት በንግድ ህግ ላይ የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሠራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ሥራ ነው ተብሎ በሕግ የሚወሰነውን ሥራ የሚሰራ ማንኛውም ሰው ነው፤

**WHWREAS,** it has become necessary to make them the preferred places that society frequents to relax and rest commercial and service provider institutions along the city's roadside light up their stand-by lights that further highlight the beauty of the area and are helpful in ensuring peace and security;

**WHWREAS,** it has become necessary to the need to proclaim by law the system of procedures under which commercial and public transport service institutions could perform their duties in the evening.

**NOW, THEREFORE,** this regulation is issued by the Cabinet of Addis Ababa City Government in accordance with Article 94 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Establishment and to Re-specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 84/2023.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as "A Regulation to make it give the Commercial and Transport Services in the Evening Regulation No. 184/2025".

### 2. Definition

In this Regulation, unless the context or the phrases otherwise requires:

1. "**City**" means Addis Ababa City;
2. "**City Government**" means Addis Ababa City Government.
3. "**Bureau**" means Addis Ababa city Government Trade Bureau;
4. **"Trader**" means anyone who does a commerce that is legally determined to be a business that does or provides services to the commercial activities listed in the Commercial Code in order to appropriate use a commerce as his or her career;

፭."**የንግድ ተቋም**" ማለት ንግድ ሥራ ፈቃድ በማውጣት በከተማው መንገድ ዳር የንግድ ሥራ የሚሰራ የንግድ መደብር ነው፤

፮. "**የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋም**" ማለት በከተማዋ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎቶች ለመስጠት በቢሮው የተመዘገበና የኦፕሬተርነት ፈቃድ የተሰጠው የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተቋም ነው፤

፯. “**ምሽት**” ማለት እንደአግባቡ ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ ፲፪ ሰዓት ድረስ ያለው ጊዜ ነው፤

፰. “**አገልግሎት ሰጪ ተቋማት**” ማለት በከተማው አስተዳደር ውስጥ በመንገድ ዳር ያሉ መንግሥታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሌሎች ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ያካትታል፤

፱. "**ሰው**" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤

፲. በዚህ ደንብ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ ደንብ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ፡-

፩. በከተማው መንገድ ዳር በሚገኙ የንግድ ተቋማት ወይም ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ፤ እና

፪. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የንግድ እና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተቋማት ግዴታ

## ፬. የንግድ ተቋማት የሥራ ጊዜ

ማንኛውም የንግድ ተቋም፡-

5. "**Commercial Institution**" means a business store that operates a business along the city's roadside by issuing a commercial license;
6. "**Public Transport Service Institution**" means a public transport service institution registered with the Bureau and licensed as an operator to provide public transport services in the City;
7. “**Evening**” means the time from evening 12:00 pm to 12:00 pm in the early morning as appropriate;
8. “**Service Institutions**” means it includes governmental and non-governmental organizations along the road in the city government and other institutions that provide services to the public;
9. "**Person**" means any physical or juridical person;
10. Any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. Scope of Application

This Regulation is in the City of Addis Ababa:

1. On commercial institutions or other service provider institutions along the city road; and
2. Shall be applicable to public transport service provider institutions.

## PART TWO
## COMMERCIAL AND PUBLIC TRANSPORT SERVICE INSTITUTIONS DUTY

## 4. Working Times of Commercial Institutions

Any Commercial Institutions:

፩. በቀኑ ክፍለ ጊዜ ሲካሄድ የነበረው የንግድ ሥራ እንደተጠበቀ ሆኖ ዘወትር ማታ ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት እስከ ምሽቱ ፫፡፴ ሰዓት ድረስ የንግድ ተቋሙን ለተገልጋይ ክፍት በማድረግ አገልግሎት መስጠት አለበት፤

፪. በምሽት ክፍለ ጊዜ የመግቢያ በሩ ዝግ በማድረግ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ የንግድ ተቋሙ ለአገልግሎት ክፍት መሆኑን የሚያሳይ በመብራት የሚሰራ ምልክት በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ ማስቀመጥ ይኖርበታል፤

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ከሥራ ባህሪያቸው አኳያ ፳፬ ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ የንግድ ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አይመለከትም፡፡

## ፭. <u>የሕዝብ ትራንስፖርት ተቋማት የሥራ ጊዜ</u>

ማንኛውም የሕዝብ ትራንስፖርት ተቋም፡-

፩. በቀኑ ክፍለ ጊዜ ሲያካሂድ የነበረው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንደተጠበቀ ሆኖ ዘወትር ማታ እስከ ምሽቱ ፬ ሰዓት ድረስ የትራንስፖርት አገልግሎት መስጠት አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ከትራንስፖርት ቢሮ በሚሰጠው ስምሪት መሠረት መሰማራት ይኖርበታል፡፡

## ፮. <u>መብራት ስለማብራት</u>

፩. አግባብ ያለው የከተማው አስፈጻሚ አካል ባወጣው የመብራት ስታንዳርድ መሰረት ማንኛውም የአገልግሎት ሰጪ ተቋም የንግድ ተቋም እና የመኖሪያ ቤት የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ማስገባት አለበት፤

፪. ማንኛውም በመንገድ ዳር ላይ የሚገኝ የንግድ ተቋም ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ ፲፪ ሰዓት ድረስ የተቋሙን የውጭ እና የውስጥ መብራት ማብራት አለበት፤

1. The commercial activities that was being run during the day session as expected and should be serviced every night from evening 6:00 pm to evening 9:30 pm by keeping the commercial institution open to a client;
2. If the entrance door is serviced by closing during the evening session, the commercial institution will have to place a lamp-operated sign in a clearly visible position, indicating that it is open for use;
3. Despite the Provision of Sub Article (1) of this Article, it does not apply to commercial or service provider institutions that provide 24 hours of service in the context of their work characteristics:

## 5. <u>Working Times of Public Transport Institutions</u>

Any Public Transport Institution:

1. The public transport service it was conducting during the day session as expected and should provide transport services every night until evening 10:00 pm;
2. It shall be engaged in accordance with the deployments from the Transport Office within the period provided by Sub Article (1) of this Article.

## 6. <u>Lighting Up</u>

1. According to a lighting standard issued by the appropriate city executive, any service provider must enter a lamp or a fasad light lamp of the front page of a building;
2. Any commercial institution or service provider located on the side of the road must light the institution’s exterior and interior lighting from evening 6:00 pm until 6:00 am in the early morning;

፫. ማንኛውም በመንገድ ዳር ላይ የሚገኝ መኖሪያ ቤት ከምሽቱ ፲፪ ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋቱ ፲፪ ሰዓት የውጭ መብራት ማብራት አለበት፡፡

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) (፫ )ድንጋጌዎች መሠረት መብራቱ የሚሰራ መሆኑን በየዕለቱ ከመምሽቱ በፊት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## ፯. <u>ተገልጋይ ስለማስተናገድ</u>

ማንኛውም የንግድ ተቋም፡-

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፬ መሰረት በምሽት ክፍለ ጊዜ ንግድ ተቋሙን ክፍት ሲያደርግ በቀኑ ክፍለ ጊዜ ሲቀርብ የነበረውን አገልግሎት ወይም ምርት በተሟላ ሁኔታ በምሽት ክፍለ ጊዜም ለተገልጋይ ማቅረብ አለበት፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በባህሪያቸው ለገበያ ቀርበው ብዙ ጊዜ ሊቆዩ የማይችሉ ወይም ለማዘጋጀት ጊዜ የሚወስዱ ሸቀጦችን ወይም ምርቶችን ለማቅረብ የማይገደድ ይሆናል፤

፫. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ ንዑስ (፩) መሠረት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ ማንኛውም ሰው በቀን ክፍለ ጊዜ በሚከፈለው ታሪፍ አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>ስለክልከላ እና አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

## ፰. <u>ክልከላ</u>

፩. ማንኛውም የንግድ ተቋም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

ሀ) ከምሽቱ ፫፡፴ ሰዓት በፊት የንግድ ተቋሙን መዝጋት፤

ለ) ለተገልጋይ ሊያቀርብ የሚችለው አገልግሎት ወይም ምርት እያለው የለም በማለት ተገልጋይ እንዳይስተናገድ ማድረግ፤

ሐ) መንገድ ዳር ያሉ ንግድ ተቋማት እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ የተቋሙን የውጭ እና የውስጥ መብራት አለማብራት፤

3. Any road side housing must be switch on the out door lighting from evening 6:00 PM until 6:00 AM in the early morning.

4. Under the Provisions of Sub Article (1) and (2) of this Article, the light must be checked before it is in the evening that it is valid.

## 7. <u>Handling the Client</u>

Any Commercial Institution:

1. Under Article 4 of this Regulation, in the evening session, when a business is keeping the institution open, it must provide a service during the evening session to the full extent of the service or product that has been offered during the day session;
2. In spite of the Provisions of Sub Article (1) of this Article, it would be unforced to provide goods or products that could not be marketed in their nature and would not be long maintained or would take time to prepare;
3. Under Sub Article (1) of Article 5 of this Regulation, anyone who provides public transport services must be served by a tariff paid during a day session:

## <u>PART THREE</u>

## <u>PROHIBITION AND ADMINISTRATIVE ACTION</u>

## 8. <u>Prohibition</u>

1. Any Commercial Institution is prohibited from performing the actions listed below:

a) Closing the commercial facility before evening 9:30 pm;

b) To avoid being handled in a client by saying that he is not having a service or product that he can offer to a server;

c) Roadside commercial institutions and service providers from evening to dawn do not illuminate the institution's exterior and interior lighting;

መ) የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ያለመስቀል እና/ወይም ያለማብራት፣

ሠ) የንግድ ተቋሙ መግቢያ በር ዝግ ሆኖ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ክፍት መሆኑን የሚያመለክት በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምልክት ያለማድረግ፡፡

፪. ማንኛውም የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድርጊቶች መፈጸም የተከለከለ ነው፡-

ሀ) ከምሽቱ ፬ ሰዓት በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ማቋረጥ ወይም ከስምሪት መውጣት ወይም የስምሪትን መስመር ማቆራረጥ፣

ለ) የከተማ አስተዳደሩ ካወጣው የትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፍ በላይ ተሳፋሪውን ማስከፈል፤

## ፱. <u>አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

፩. ማንኛውም የንግድ ተቋም ወይም አገልግሎት ሰጪ ተቋም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገጉትን ክልከላዎች ተላልፎ ሲገኝ በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ እንዲያስተካክል ቢሮው የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ማስተካከል ካልቻለ ቢሮው ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው የቅጣት ሰንጠረዥ መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣቱን እንዲከፍል ማስታወቂያ ይሰጠዋል፤

፫. የንግድ ተቋሙ በአስተዳደራዊ ቅጣቱ መታረም ሳይችል ቀርቶ በተደጋጋሚ ጥፋቶችን የሚፈጽም ከሆነ በሰንጠረዥ ላይ የተጠቀሰውን የገንዘብ ቅጣት፡-

d) Building's front part light or Fasad's light lamp without cross and/or incandescent light;

e) Without an electrically operated signal indicating that the entrance to the commercial institution is open if it is closed and serviced.

2. Any public transport service provider institution is prohibited from performing the actions listed below:

a) Interruption of transport services before evening 10:00 pm, or withdrawal from the deployment or cutting off the deployment line;

b) Charging the passenger more than the transport service tariff the city government has enacted.

## 9. <u>Administrative Action</u>

1. Any commercial institution or service provider is given written warning by the Bureau to fix the prohibitions imposed by the Sub Article (1) of Article 8 of this Regulation within twenty-four hours of its violation;
2. If he fails to correct it under Sub Article (1) of this Article, the Bureau is given notice to pay the administrative fine under the fine table attached to this rule.
3. If the commercial institution is unable to be corrected by the administrative fine, and will frequently commit misconduct, the fine mentioned in the table is:

ሀ) ለሁለተኛ ጊዜ ጥፋት ከፈጸመ ፩/፫ (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፣

ለ) ለሶስተኛ ጊዜ ካጠፋ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሀ) ላይ የተሰጠው ቅጣት (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፣

ሐ) ለአራተኛ ጊዜ ካጠፋ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ለ) ላይ የተሰጠው ቅጣት ፩/፫ (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፣

መ) ለአምስተኛ ጊዜ ካጠፋ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ተራ ፊደል (ሐ) ላይ የተሰጠው ቅጣት (አንድ ሦስተኛ) ተጨምሮ እንዲቀጣ ይደረጋል፣

ሠ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የገንዘብ ቅጣት ተቀጥቶ ማረም ካልቻለ ቢሮው የንግድ ሥራ ፈቃዱን ያግዳል፤ በእግዱ መሠረት ችግሩ ካልታረመ የንግድ ፈቃዱን ይሰርዛል፤

፬. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የንግድ ፈቃዱ የተሰረዘበት ሰው የንግድ ተቋሙ የንግድ ሥራ እያከናወነ የሚገኘው በመንግስት ቤት ውስጥ ከሆነ ቢሮው ቤቱን ለሚያስተዳድርው አካል የንግድ ሥራ ፈቃዱ የተሰረዘ መሆኑን መረጃውን ያስተላልፋል፤

፭. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት መረጃው የደረሰው አስፈጻሚ አካል ቤቱን ከተከራየው ሰው ጋር ያደረገውን ውል ያቋርጣል፤ ውሉ የተቋረጠ መሆኑንም ለተዋዋዩ ያሳውቃል፤ ቤቱንም ይረከባል፤

a) If commits a second fault, then 1/3 (one-third) is added and punished;

b) If spends a third time, the penalty 1/3 (one-third) given in this Article ordinary letter (a) is added and fined, with the exception that the penalty be imposed;

c) If spends a fourth time, the penalty 1/3 (one-third) given in this Article ordinary letter (b) is added and fined;

d) If spends a fifth time, the penalty (one-third) given in the ordinary letter (c) of this Article is added and fined;

e) Under this Sub Article, if he is not able to be fined and rectified, the Bureau suspends his business license; under the ban, if the problem is not corrected, his commercial license will be revoked.

4. According to Sub Article (3) of this Article, the person whose commercial license was revoked would convey the information that if the commercial institution was doing commercial activities in the government house, the Bureau had informed for the institution that operated the house, its commercial license is revoked;

5. According to Sub Article (4) of this Article, the executor who received the information would terminate the contract that the house had been made with the person who rented it, and inform the contracting party that the contract had been terminated, and take over the house;

፮. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ቢሮ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገጉትን ክልከላዎች ተላልፎ ሲገኝ በዚህ ደንብ አባሪ በተደረገው ሰንጠረዥ መሠረት አስተዳደራዊ ቅጣቱን እንዲከፍል ማስታወቂያ ይሰጠዋል፣

፯. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ተቋሙ በአስተዳደራዊ ቅጣቱ መታረም ሳይችል ቀርቶ በተደጋጋሚ ጥፋቶችን የሚፈጽም ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ተፈጻሚ ይደረጋል፡፡

**፲. <u>አስተዳደራዊ እርምጃ አወሳሰድ</u>**

፩. በዚህ ደንብ መሠረት አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት የተጣለበት ማንኛውም ሰው የተሰጠውን አስተዳደራዊ ቅጣት ማስታወቂያ ወረቀት በመያዝ ወዲያውኑ ጥፋቱ በተፈፀመበት አካባቢ በሚገኘው የወረዳ ንግድ ጽህፈት ቤት ወይም ትራንስፖርት ቢሮ ቀርቦ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መክፈያ ዘዴ በሶስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ቅጣቱን መፈጸም አለበት፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት አስተዳደራዊ መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ሰው የተጣለበትን የቅጣት ገንዘብ መጠን እጥፍ እንዲከፍል ይደረጋል፣

፫. የቅጣት ማስታወቂያ ለመቀበል ፍቃደኛ ካልሆነ እንደተቀበለ ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፣

፬. ቢሮው ወይም የትራንስፖርት ቢሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት መቀጫውን ገቢ ያላደረገ ማንኛውም ሰው ላይ ክስ እንዲቀርብ ለከተማው አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ማስረጃውን አደራጅቶ ይልካል፡፡

6. The Bureau of Transport of the City of Addis Ababa is given notice to pay the administrative fine under the table attached to this regulation when it is found to have circumvented the prohibitions imposed by the Sub Article (2) of Article 8 of this regulation;
7. If the public transport service provider institution is unable to be corrected by the administrative fine, and even frequently commits faults, it is enforced under Sub Article (3) of this Article.

**10. <u>Taking Administrative Action</u>**

1. Under this Regulation, anyone who is subject to an administrative fine must carry the notice sheet of a given administrative fine and immediately appear at the woreda trade office or transport bureau in the area where the fault was committed, or perform the fine by making money in three consecutive business days through an electronic payment scheme;
2. According to Sub Article (1) of this Article, a person who does not making money, the administrative fine is required to pay double the amount of fined money imposed;
3. If he refuses to accept a notice of fault, he is deemed to have received and shall be enforced under the Provision of Sub Article (2) of this Article;
4. The Bureau or the Bureau of Transportation organizes and sends the evidence to the City Administrative Justice Bureau for prosecution against anyone who did not making the fine under Sub Article (2) of this Article.

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፩.ቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ

፩. ቢሮው ወይም የትራንስፖርት ቢሮ በሚሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ውሳኔው በተሰጠው በሦስት ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ውሳኔውን ለሰጠው አስፈጻሚ አካል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላል፤

፪. ቅሬታውን የተቀበለው ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን ከተቀበለበት ቀን ጀምሮ በሚኖሩት ፭ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ጉዳዩን መርምሮ የውሳኔ ሀሳቡን ለቢሮው ወይም ለትራንስፖርት ቢሮ የበላይ ኃላፊ ማቅረብ አለበት፤

፫. የውሳኔ ሀሳብ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ በ፭ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውሰጥ ውሳኔ ይሰጣል፤

፬. የበላይ ኃላፊው የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤

፭. ቅሬታ አቅራቢው ላቀረበው ቅሬታ ውሳኔ እስከተሰጠ ድረስ ቅጣቱ ከመፈጸም ታግዶ ይቆያል፤

፮. የአስፈጻሚ አካሉ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል፡፡

### ፲፪.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ ለማስፈጸም ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### ፲፫.ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ህጎች

ይህንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም የከተማ ካቢኔ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 11. Grievance and Petition Handling Procedure

1. Anyone who is complaining about the administrative decision of the Bureau or the Bureau of Transportation may submit a grievance to the executive body's grievance committee, which has made the grievance decision within three consecutive days of the decision;
2. The grievance committee, which has accepted the grievance, must investigate the matter during the 5 consecutive working days from the date of receipt of the grievance and submit the recommendation to the Bureau or the Head of the Bureau of Transportation;
3. A recommendation is made by the Head of the Bureau who will make a decision on 5 consecutive working days;
4. The decision of the Head would be final;
5. The fine will remain suspended from carrying out until a decision is made for the grievance filed by the complainant;
6. Anyone who is disappointed by the decision of the head of the executive body may petition to the competent court.

### 12. Duty to Cooperate

Everyone has the duty to cooperate when asked in the enforcement of this regulation.

### 13. Inapplicable Laws

Any regulation, directive or customary practice of the City Cabinet does not apply to issues covered by this Regulation.

## ፲፬. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከየካቲት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፱ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም.**

**አዳነች አቤቤ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ**

## 14. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force as of this 8th of March, 2025.

**Done at Addis Ababa, this 8th of March, 2025.**

**Adanech Abiebie Desa**
**Mayor of Addis Ababa City**

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ማስከፈል፡፡ | |

## አባሪ፡ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የጥፋቱ ዓይነት | የቅጣት ክፍያ ለአንድ ጊዜ ጥፋት በብር መጠን |
|---|---|---|
| ፩ | ከምሽቱ ፫ ሰዓት ከ፴ በፊት የንግድ ተቋሙን መዝጋት፤ | ፲ ሺ |
| ፪ | ለተገልጋይ ሊያቀርብ የሚችለው አገልግሎት ወይም ምርት እያለው የለም በማለት ተገልጋይ እንዳይስተናገድ ማድረግ፤ | ፲ ሺ |
| ፫ | መንገድ ዳር ያሉ ንግድ ተቋማት እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ከምሽት እስከ ንጋት ድረስ የተቋሙን የውጭ እና የውስጥ መብራት አለማብራት፤ | ፯ ሺ |
| ፬ | የሕንጻ የፊተኛው ገጽ መብራት ወይም የፋሳድ ላይት መብራት ያለመስቀል እና/ወይም ያለማብራት፣ | ፭ ሺ |
| ፭ | የንግድ ተቋሙ መግቢያ በር ዝግ ሆኖ አገልግሎት የሚሰጥ ከሆነ ክፍት መሆኑን የሚያመለክት በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምልክት ያለማድረግ፡፡ | ፭ ሺ |
| ፮ | ከምሽቱ ፬ ሰዓት በፊት የትራንስፖርት አገልግሎት ማቋረጥ ወይም ከስምሪት መውጣት ወይም የስምሪትን መስመር ማቆራረጥ፣ | ፭ ሺ |
| ፯ | የከተማ አስተዳደሩ ካወጣው የትራንስፖርት አገልግሎት ታሪፊ በላይ ተሳፋሪውን | ፭ ሺ |

## Annex: Administrative Fine Table

| No | The Type of Fault | Penalty Fee for a Single Fault in the amount of Birr |
|---|---|---|
| 1 | Closure of the Commercial Institution before evening 9:30 pm | 10,000.00 |
| 2 | To avoid being hosted in a client by saying that the service or product he can provide to a client is not there while he has it. | 10,000.00 |
| 3 | Roadside commercial institution and service providers from late evening to early morning do not illuminate the institution's exterior and interior lighting. | 7,000.00 |
| 4 | A building's front part lamp or a Fasad Light Lamp without cross or/or illumination. | 5,000.00 |
| 5 | Without an electrically operated signal indicating that the entrance to the commercial institution is open if it is closed and serviced | 5,000.00 |
| 6 | Before evening 10:00 pm, the withdrawal of transport services or withdrawal from the deployment or the cutting of the deployment line occurred. | 5,000.00 |
| 7 | Charging the passenger more than the | 5,000.00 |

| | | |
|---|---|---|
| | transportation services Tariff issued by the city government. | |